## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

## ልሣነ ህግ-ጋዜጣ

-----ዓመት ቁጥር------ አሶሳ ------/ 2014 ዓ.ም

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ አዋጅ

## አዋጅ ቁጥር 181 /2014 ዓ.ም

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 170 /2012 ዓ.ም እንደገና ለማሻሻል የወጣ

## አዋጅ ቁጥር 181/2014ዓ.ም

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አከካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 170/2012 ዓ.ም እንደገና ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የአካባቢ አስተዳደሮች የተሰጣቸውን ራስን በራስ የማስተዳደር ተግባር ተጠቅመው ህብረተሰቡን በማነቃነቅ የህዝቡን ተሳትፎና የውሳኔ ሰጪነት ሚናን በማጉልበት በሰው ኃይል፣ በበጀትና በአሠራር ራሳቸውን በማጠናከር ለልማቱ መፋጠንና ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

የአከባቢ አስተዳደሮች ካላቸዉ የቆዳ ስፋት፣ የህዝብ ብዛት፣ የህዝብን ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ አንጻር ለህዝብ የሚሰጡትን አግልግሎት ተደራሽ በማድረግና ለአስተዳደር ምቹ በማድረግ የህዝብ  መልካም አሳተዳደር ችግሮችን መፍታት ጠቀሜታዉ የጎላ በመሆኑ፤

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3.1፣ 3(3) 2 ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

## አንቀጽ 1

## አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ *"የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 170/2012 እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር------/2014 ዓ.ም (ማሻሻያ)"* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## አንቀጽ 2

## ማሻሻያ

1. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 170/2012 ዓ.ም አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ሀ" አሶሳ ወረዳ የሚለዉ ተሰርዞ፤

"ሀ" *ኡራ ወረዳ* በሚል በመተካት ወረዳው የሚከተሉት ቀበሌዎች እንዲኖሩት ተደርገዋል፡-

| ተ.ቁ | የቀበሌው ስም | ተ.ቁ | የቀበሌው ስም | ተ.ቁ | የቀበሌው ስም | ተ.ቁ | የቀበሌው ስም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | *አጎሌ* | 12 | *አፈደሆሾ* | 23 | *አምባ 1* | 34 | *ቁጥር 15* |
| 2 | *አቡሎ* | 13 | *ቤልሚሊ* | 24 | *አምባ 2* | 35 | *ሆሃ 18* |
| 3 | *ቁሽመንገል* | 14 | *ፀንፀሀሉ* | 25 | *አምባ 3* | 36 | *ሠልጋ 19* |
| 4 | *ዬዬ አዱርኑኑ* | 15 | *ባሻ-ቡዳ* | 26 | *አምባ 4* | 37 | *ሠልጋ 20* |
| 5 | *አጉሻ* | 16 | *ዳቡስ-አድምባቆ* | 27 | *አምባ 5* | 38 | *ሠልጋ 21* |
| 6 | *ጉምባ* | 17 | *ሙጉፋዴ* | 28 | *አምባ 6* | 39 | *ሠልጋ 22* |
| 7 | *አቁዱ-ቱመት* | 18 | *ኡደባ* | 29 | *አምባ 7* | 40 | *ሠልጋ 23* |
| 8 | *ኡራ* | 19 | *ቁቆ* | 30 | *አምባ 8* | 41 | *ሠልጋ 24* |
| 9 | *ሩበዩ* | 20 | *ዳሳ-ቤልጉንዲ* | 31 | *አምባ 9* | | |
| 10 | *ባሮ* | 21 | *ጠርፈዳር* | 32 | *አምባ 10* | | |
| 11 | *ማናጌ-ሰልጋ* | 22 | *ፋለዳሩ* | 33 | *አምባ 11* | | |

2. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 170/2012 ዓ.ም አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ "ዘ" ቀጥሎ እንደሚከተለዉ ፊደል ተራ "የ" አብረሃም ወረዳ ተጨምሯል፡፡

" የ " አብረሃም ወረዳ በመጨመር ወረዳው የሚከተሉት ቀበሌዎች እንዲኖሩት ተደርገዋል፡-

| ተ.ቁ | የቀበሌው ስም | ተ.ቁ | የቀበሌው ስም | ተ.ቁ | የቀበሌው ስም | ተ.ቁ | የቀበሌው ስም |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አሀንሻ | 12 | ሸርቆሌ ኢንጂ | 23 | አምባ 12 | 34 | መገሌ 32 |
| 2 | ገንገን | 13 | ሸርቆሌ አሆፌንዱ | 24 | አምባ 13 | 35 | መገሌ 33 |
| 3 | ኮመሽጋ | 14 | ቁሽመጋኒ | 25 | አምባ 14 | 36 | መገሌ 34 |
| 4 | ጋምቤላ | 15 | ቡዱር | 26 | አምባ 17 | 37 | መገሌ 35 |
| 5 | ሩባሳገዳ | 16 | ፋፋር | 27 | ኮመሽጋ 25 | 38 | መገሌ 36 |
| 6 | ቡልድግሉ | 17 | ቡልዳደኔ | 28 | ኮመሽጋ 26 | 39 | መገሌ 37 |
| 7 | አፋሲዝም | 18 | አጤጦ አንጉላሉ | 29 | ኮመሽጋ 27 | 40 | መገሌ 38 |
| 8 | ያምባሲዝም | 19 | ጎልፃሃ | 30 | ኮመሽጋ 28 | 41 | መገሌ 39 |
| 9 | አፈ-መገሌ | 20 | አጤጦ - ሰልጋ | 31 | መገሌ 29 | | |
| 10 | አባንዴ ምንግዳ | 21 | ኢንዚሸደሪያ | 32 | መገሌ 30 | | |
| 11 | አብራሃሞ | 22 | ጋምቢሺሪ | 33 | መገሌ 31 | | |

3. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 170/2012 ዓ.ም አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 ፊደል ተራ "ሀ" ላይ የተዘረዘሩት የቀበሌ ዝርዝር ሙሉ ለሙሉ በዚህ አዋጅ ተሰርዟል፡፡

## አንቀጽ 3

ይህ አዋጅ የክልሉ ምክር ቤት ካፀደቀበት ከ-----------/2014 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

አሻደሊ ሃሰን አልአጀብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት

-------/2014 ዓ.ም

አሶሳ፣